# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 1 ቁጥር 2 ታህሳስ ፳፫ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም.

## 1953 "ታህሳስ ግርግር" 53 ዓመቱ



መንግሥቱ ነዋይ ግርማሜ ነዋይ
Mengistu Neway Girmame Neway

"ዛሬ መኖራችሁን በማየቴ ነገ መሞታችሁን ረስታችሁ አሜን ብላችሁ ቀናችሁን በማስተላለፍ በመገደዳችሁ በእኔ ላይ ሳትፈርዱ በራሳችሁ ላይ የፈረዳችሁ መሆናችሁን አላስተዋላችሁም፡፡ እኔ የተነሳሁት ከትክክለኛ ህግና ከህሊናችሁ ውጭ ለመፍረድ እንዳትገደዱ ለማድረግ ነበር፡፡ በአጭሩ በእኔ ላይ ለመፍረድ የቸኮላችሁትን ያህል አስር እና አስራ አምሰት ዓመት በቀጠሮ የምታጉላሉትን ህዝብ ጉዳይ እንደዚህ አፋጥናችሁ ብትመለከቱትና ብትሸኙት ኖሮ የእኔ መነሳት ባላስፈለገም ነበር፡፡" ብርጋዴል ጀነራል መንግስቱ ነዋይ።

**በኢትዮጵያ መንግስት ታሪክ ውስጥ የታህሳሱ 1953 ዓ.ም. መፈንቅለ መንግስት ሙካራ በዓይነቱ እና በዘመናዊነቱ የተለየ ነበር።**

**ስለምን! የታህሳሱ ንቅናቄ የሆነው በኃይለ ሥላሴ መንግስት የዘመኑ ስልጣኔ ወደ አገሪቱ እየገባ ነው አገሪቱ በስልጣኔ ጎዳና እተራመደች ነው፣ በሚባልበት ግዜ መሆኑ ነው።**

**ይሁን እንጂ፣ የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስት እያስገባ ነው የተባለለት ሥልጣኔ፣ በአገሪቱ ላይ የተፈጠረውን የህብረተሰብና የምጣኔ ሀብት ይዘት መዛባት ምክንያት ያልተለወጠው የጥንቱ የጌታና አሽከር የህብረተሰብ ግንኙነቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የፈጠረውን ቅራኔ መሸከም እያቃተው እንደመጣና ይብሱን የመንግስትና የአገሪቱን 40% የለም መሬት ባለቤት የነበረው የዘመኑ ባለ ሲሶ መንግስት የሃይማኖት ተቋም የራሳቸውን የግል ጥቅም ለማስከበር የደባ ግንባር በህዝቡ ላይ በመፍጠራቸው ማነቆ ሆኖ አገሪቱ እዛው ያለችበት ትረግጥ ነበረ። ይህንን ባለህበት እርገጥ ጉዞ ከተመለከቱት ጥቂት የለውጥ ስነ ልቦና ከነበራቸው ደፋር የአገሪቱዋ ምሁራን መሀል የታህሳሱን መፈንቅለ መንግስት በመሪ ተዋንያንነት የመሩትን ብርጋዴል ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ እና ወንድማቸው አቶ ግርማሜ ነዋይን ልብ ይሏል።**

**የታህሳስ 1953ቱ ንቅናቄ፣ ለመጀመሪያ ግዜ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ላይ አዲስ ምዕራፍ በመክፈት ከጥንቱ የፊውዳላዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት መንግስት ይልቅ በአማራጭ ሌላ ዘመናዊ የመንግስት ስርዓት እንዳለ የኃይለ ሥላሴም መንግስት እንደሚሉት፣ መለኮታዊ ሳይሆን፣ የሚገሰስ፣ የሚደፈር፣ መንግሥት እንደሆነ በማሳየቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንቅቷል።**

በሌላ ጎኑም የዘመኑን ሥልጣኔ ወደ አገር ቤት ለማምጣት ብርቱ ጥረት አርጓል ለሚባለው የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስትም ይህ የታህሳሱ ንቅናቄ፡ በመንግስት እና በሕዝብ መሃል ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ መውደቁን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል።

እነሆ! የታህሳስን ንቅናቄን (ግርግር)፡ በየዓመቱ እናስታውሰዋለን። ታዲያ! ለዚህ የታሪክ ማስታወሻ፡ ከዚህ ከ"ያ ትውልድ ተቋም" ዝግጅት ክፍል (www.yatewild.com , www.yatewild.org ) የሚከተለውን ጽሁፍ ስናቀርብ፡ በህዝብ እጅ ካሉት የዛ ዘመን ማስታወሻ ውጭ፡ አዲስ ዜና ይዘን ባንቀርብም እንኳ: አዕምሮን ለመጎንተል ያህል ያለንን እነሆ።

ዓፄ ኃ/ሥላሴ በ40 ዓመታት አገዛዝ ዘመናቸው ለሀገሪቷ የሠሩት በጎ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በተለይ ሀገሪቷን ተብትቦ የያዘውን ባላባታዊ አስተዳደር የመሬት ስሪትን በማስተካከል ወደ ዘመናዊና ፍትህ እሰፈነበት አስተዳደር መለወጥ ስለተሳናቸው በየጊዜው ብቅ ብቅ ያሉ አካባቢያዊ ጥያቄዎችና ተቃውሞዎች ሕዝባዊና ሀገራዊ መልክ ይዘውና ዓመጽ ወልደው ንጉሳዊው አገዛዝ ሙሉ በሙሉ እንዲገረሰስ ሆኗል።

በዓፄ ኃ/ሥላሴ ላይ የተነሳው የ1953ቱ ተቃውሞ የአምስት ዓመት የአርበኞች ትግል ተቀጽላነት ባሕሪ አለው። ጀግኖች አርበኞች አምስቱን ዓመት ተፋልመውና ተጋድለው ኢትዮጵያን ከወራሪው ጣልያን ነፃ ካወጡ በኋላ በንጉሡ ዘንድ የተወሰደው አንዳንድ አርበኞችን የማግለል ሁኔታ በአርበኞች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል። "ኢትዮጵያ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" እንደተባለው በንጉሡ አገዛዝ ውስጥ ባንዳዎች ያገኙት ሹመትና ማዕረግ ይበልጥ ቅሬታውን አባባሰው። የዚህም ውጤት በንጉሡ አገዛዝ ላይ ያመጹ ሦስት የቀድሞ አርበኞች ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህና፣ ብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት በተለያየ ጊዜ መስዋዕትነት ሊከፍሉ ተገደዋል። ንጉሡ ለስልጣኔ ያሰጋኛል ያሉትን አንዱን በሹመት ስም ሲያርቁ፤ ሌላውን በጋብቻ ስም ሲይዙ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ቢጥሩም በ1953 ዓ.ም. የለውጥ ደወሉን ያሳየው የታህሳስ ግርግር ከ13 ዓመት በኋላ በ1966 የካቲት አብዮት የዓፄ ኃ/ሥላሴን ፊውዳላዊ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን በሺህ ዓመታት የሚቆጠረውን ሥርወ መንግስት ጭምር ነው ያስወገደው።

ጄነራል መንግስቱ ነዋይ፡ ከአባታቸው ከአለቃ ነዋይ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ላቀች፡ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በቅዱስ ጊዮርጊስ የስዊሶች ትምህርት ቤት ተማሩ።

ብርጋዴል ጄነራል መንግሥቱ ነዋይ ከ1928 ዓ.ም. በፊት በካዴትነት ይሰለጥኑ የነበሩትና በጠላት ጦርነት ወቅት የጥቁር አንበሳን ድርጅት አቋቁመው ጠላትን የተፋለሙት የወጣት አርበኞች ትውልድ አባል ነው።

የ1953 ንቅናቄ ዋናው አቀንቃኝ በይበልጥ የሚነገርለት ወንድሙ ግርማሜ ነዋይ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ (ከ1848 እስከ 1966) በሚለው መጽሐፋቸው እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

አገላለጽ “ግርማሜ በቅድመ 1928ቱ ተራማጅ ምሁራንና በ1950ዎቹ ዓመታት ብቅ ባሉት ሥርነቀል ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎች መካከል የነበረ ድልድይ ነው ማለት ይቻላል።”

በ1940ዎቹ አጋማሽና በ1950ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት በኢትዮጵያ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እንዲመጣ አበክረው ከሚሹ ወጣቶች መካከል አንደኛው ግርማሜ ነዋይ ነበር። አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎ በሚገኘው ገዳም ሰፈር በመባል በሚጠራው አካባቢ በ1916 ዓ.ም. የአራዳ ጊዮርጊስ ካህን ከነበሩት አባቱ አለቃ ነዋይና ከእናቱ ወ/ሮ ላቀች፤ ግርማሜ ነዋይ ተወለደ።

በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግስት የንጉሠ ነገስቱ የክብር ዘብ አዛዥ የነበሩት የብርጋዴል ጀነራል መንግስቱ ነዋይ ስምንት ዓመት ታናሽ የሆነው ግርማሜ ነዋይ አብዛኛውን ዕድሜውን ያሳለፈው ለዕውቀት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በትምህርት ነበር። ፋሺስት ኢጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት በዚያን ዘመን ትምህርቱን ቀጥሎ የነበረው ግርማሜ ከ1933 ዓ.ም. የሀገራዊ ነፃነት ማግስት ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በመዝለቅ ትምህርቱን ተከታተለ። በቀጣይነትም በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮተቤ) የሀገር ቤት ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ አሜሪካ ተጉዞ የመጀመሪያ ድግሪውን በፖለቲካል ሳይንስ ከዊስኮንሲን ዩንቨርስቲ፣ ቀጥሎ ሁለተኛውንና የማስተርስ ዲግሪውን ከኮሎምቢያ ዩንቨርስቲ አግኝቷል። የመመረቂያ ጽሁፍ ርዕሱም “በኬናውያን ያለ የቅኝ ገዥዎች አስተዳደር መመሪያ ያስከተለው ችግር” በሚል ነበር።

ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ በመጽሐፋቸው፤ ግርማሜን ቀደም ካሉት ምሁራን የሚለየው በሁለት ነገሮች ነው ይሉታል። “አንደኛው ውጭ ሀገር ቆይቶ አንዳንድ ነገሮችን ቀስሞ መመለስ ብቻ ሳይሆን መደበኛ ትምህርት ተከታትሎ ለዚህም ምስክርነት ዲግሪውን ይዞ በመመለሱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የላቀ የድርጅት ስሜት ማሳየቱ ነው።” በማለት ይገልጹታል። አሜሪካ ሀገር በነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ከመሆኑ በተጨማሪ ሀገር ቤት ከተመለሰም በኋላ የኮተቤን ምሩቃን በስውር አሰባስቦ ማኅበር በማቋቋም የዚሁ ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆኖ አገልግሏል።

ግርማሜ በ1946 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ በሀገር ግዛት ሚንስቴር መስሪያ ቤት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በ1950 ዓ.ም. ወደ ጡረታ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ተዛውሮ ሥራውን ቀጥሏል። በዚህም ስራው መጀመሪያ ከራስ መስፍን ስለሺ ጋር ቀጥሎ ከራስ አበበ ጋር ተገናኝቶ ሁለቱም ለለውጥ የማይመቹ፡ የሚያቀርበውን የለውጥ ሀሳብ የማይደግፉ እንዲያውም ተራማጅ በማለት ከስራው ያገሉት ጀመር። በሠራባቸው የሚንስቴር መስሪያቤቶችም በተመለከታቸው ከፍተኛ ቢሮክራሲያዊና ባላባታዊ አሰራሮች እጅግ አድርጎ ይበሳጭ ነበር። በመሆኑም በንጉሡ የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ከፍተኛ ትችት ይሰነዝር ጀመር። መንግሥት ይህንን አዝማምያውን አልወደደለትም። በተከታታይ በስውር ግዞት የሩቅ ግዛቶች አስተዳዳሪ እየተደረገ ተሾመ፤ መጀመሪያ ወላይታ፡ ኋላ ጅጅጋ። ግርማሜ እነዚህን ቦታዎች የፍታዊ አስተዳደር ሙከራ ጣቢያዎች አደረጋቸው። የወላይታ አስተዳዳሪ በነበረበት ጊዜ በገባርነትና በጭሰኝነት ለሚማቅቁት የኢትዮጵያውያን ልጆች የነበረው መቆርቆርና

ወገናዊነት ስሜት ይበልጡን እየጨመረ መጣ። የእርሻ መሬት ላጡ ያካባቢው ተወላጆች መሬትን በመሸንሸንና በማከፋፈል ዝቅ ብሎ ከደሃው ገበሬ ጋር መገናኘት መቻሉ ከገበሬው ያገኝ የነበረው ወንድማዊና አባታዊ ፍቅር በንጉሱ ባላባትና መኳንንት ዘንድ አልተወደደለትም። በጅጅጋም የነዋሪውን ሕይወት ለማሻሻል በወሰዳቸው እርምጃዎች ከፍተኛ ተወዳጅነትን አገኘ። ሆኖም መንግሥት በዚህ በጠረፍ አስተዳደሩም ጣልቃ እየገባበት ያደናቅፈው ጀመር። ያኔ ነው ማዕከሉን መለወጥ አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑን ተረድቶ ወንድሙን ለዚህ ዓላማ ማነሳሳት የጀመረው።

ግርማሜ ነዋይ በጊዜው ኢትዮጵያ ካሏት እጅግ በጣም ጥቂት ምሁራን አንዱ እንደመሆኑ መጠን በተጨማሪም የወንድሙ ብርጋዴል ጄነራል መንግስቱ ነዋይ በንጉሡ አገዛዝ ውስጥ ካለው ከፍተኛ ቦታ አንፃር ለግል ሕይወታቸው ተከብረውና አንቱ ተብለው መኖር አላቃታቸውም። በሥርዓቱ ብልሹ የባላባታዊ አገዛዝ ውስጥ ተዘፍቀው፤ እራሳቸውን ወድደውና አድፍጠው የግፍ አገዛዙ ተሸካሚዎች ከመሆን አልፈው እንደሌሎቹ ግፈኞች መሆን፣ ገበሬውን ማሰቃየት፣ ወታደሩን መርገጥ፣ ጉቦኝነትን ማበረታታት፣ ሕፃናትን ማደንቆር፣ ደሀን ማስራብ አቅቷቸው አይደለም። የሕዝብ ብሶት፣ በሀገሪቷ የሰፈነው ባላባታዊ መብት ረገጣ፣ የፍትህ እጦት፣ ብልሹ ፊውዳላዊ አስተዳደር ሀገሪቷን በልማት ወደ ኋላ ማስቀረቱን ሕዝቡን ለረሃብ፣ ድንቁርናና ድህነት መዳረጉን ዓይተውና ተገንዝበው ከታች ያለውን ማስተካከል የትም ሊያራምድ እንደማይችል ተረድተው ሥርዓቱ እራሱ መናድ እንዳለበት አልመው የተነሱ የአገዛዙ ባለሥልጣናት የሕዝብ ወገኖች ነበሩ።

የታህሳስ ግርግርን የመሩት ወንድማማቾች በዓላማ ግልጽነትም ሆነ በአደረጃጀት ብቃት ጉድለት እንደነበረው የሚተቹ ቢኖሩም የሀገሪቷን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች ይዞ የተነሳ ነበር። ንጉሡ፣ ባላባቱና መኳንንቱ መፈንቅለ መንግሥቱ የጥቂት ውለታ ቢሶች ሤራ እንጂ ማኅበራዊ መሠረት ያለው የለውጥ እንቅስቃሴ ደወል መሆኑን ሊቀበሉ ባለመቻላቸውና በቀጣይነትም ሥልጣናቸውን ማጥበቅ እንጂ የሕዝቡንና የአርሶ አደሩን ብሶት ከቁብ ባለመቁጠራቸው ግርማሜና መንግሥቱ የደወሉት ደወል የካቲት 1966 ተደወለ። ንጉሡ ከታህሳሱ ንቅናቄ በኋላ እንኳ ድህነትን፣ ረሃብን፣ ድንቁርናን፣ በሽታን፣ ኋላ ቀርነትን ሊቀርፉ ባለመቻላቸው፣ ፍታዊ የአስተዳደር መረብ ሊዘረጉ ስለተሳናቸው፤ 13 ዓመት ቆጥሮ ሕዝባዊ ማህበል ዋጣቸው። “ስዩመ እግዚሐብሔር” ሀገር ለማስራብ፣ በስልጣን ለመኖር የተሰጠ ማስፈራሪያ እንዳልሆነ የጭቁን ብሶት የወለደው አብዮት ፊውዳላዊውን ሥርዓት በአስከፊው መልኩ በጣጠሰው።

ከንጉሠ ነገስቱ መንግሥት ባለስልጣኖች መካከል አንዱ ሆኖ በመቀጠል የሀገሩንና የወገኑን ጉስቁልና ከማሰብ ይልቅ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ወደ ዕድገትና ብልጽግና የሚመራቸው ፈር ቀዳጅ ለውጥ ያሻል በሚል እምነት ታላቅ ወንድሙን ብርጋዴል ጄነራል መንግስቱ ነዋይንና ዓላማውን የሚደግፉትን ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር የ1953 ዓ.ም. ወርሃ ታህሳስ የለውጥ እንቅስቃሴን መራ። ግርማሜ ነዋይ።

ታህሳስ 4 ቀን 1953 ዓ.ም.፦

በዚህ ማታ ጄነራል መንግስቱ 1ኛ. ጀነራል ጽጌ ዲቡን 2ኛ. ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን እቤታቸው እራት ግብዣ ጠርተው የጦር ሠራዊት በንጉሱ ላይ ማመጹን ነግረው ይህንን ዓመጽ መከላከል እንዳለባቸው በማስገንዘብ የንቅናቄውን ፕላን ይነግሯቸዋል።

በፕላኑም መሰረት 1ኛ. የሬዲዎ ጣቢያው 2ኛ. ቤተ መንግስቱ 3ኛ. አዲስ አበባ በ10 የጦር ቀጠና መጠበቁን 4ኛ. 21 የንጉሱ ሹማምንትና ሚንስቴሮች በቁጥጥር ስር መሆን ተነገረ።

ታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም.፦

ጠዋት አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ኃይለ ሥላሴ የሬዲዎ መግለጫ ሰጡ

ታህሳስ 6 ቀን 1953 ዓ.ም. የንቅናቄው ስህተት፦ ጄነራል መርድ መንገሻ ባለ መያዛቸው ጦር ሠራዊቱን ማዘጋጀት መጀመራቸው እና የንጉሱ ታመኝ ወገኖች እና ቤተ ክህነት ሕዝቡን ለንጉሰ ነገስቱ እንዲታመን መስበክ ጀመሩ። ይህም በሕዝቡና በለውጥ ደጋፊው ላይ ብዥታ መፍጠር ቻለ።

ታህሳስ 7 ቀን 1953 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አየር ኃይል ወረቀት በመርጨቱ ንቅናቄውን ይከላከላል የተባለው የክብር ዘበኛ ከብርጋዴል ጄነራል መንግስቱ የተነገረው ዜና ስህተት መሆኑን በማወቁ መበታን ጀመረ።

ቀጥሎም የንቅናቄው መሪዎች ያሉበት በመከበቡ፣ በቁጥጥር ስር እነበሩት 21 የንጉሱ ባለ ስልጣኖች ላይ የሞት ቅጣት ሰጥተው ሁሉም በየአቅጣጫው አፈገፈጉ። በተደረገውም የተኩስ ልውውጥ፣ ጀነራል ጽጌ ዲቡ እና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ሲሰው፣ ጄነራል መንግስቱ እና ግርማሜ፣ ከአዲስ አበባ ወጣ እንዳሉ በመከበባቸው፣ የጀነራሉ እጅ እንዳይያዝ፣ የሰጋው ግርማሜ በተኮሰው ተኩስ፣ ጄነራሉ የግራ ዓይናቸው ስር ተመተው፣ ሲወድቁ የሞቱ ስለ መሰለው እራሱን ሰውቷል።

በተወለደ 36ኛ ዓመቱ መጨረሻ ህይወቱን እስካጣበት ድረስ በተራማጅነቱ የጸናው ግርማሜ ነዋይ ታህሳስ 4 ቀን ምሽት እስከ ታህሳስ 5 ቀን ምሽት የዘለቀው የለውጥ ንቅናቄ አልሳካ ካለ በኋላ ታህሳስ 15 ቀን 1953 ዓ.ም. ዝቋላ አቅራቢያ በምትገኘው ድሬ ጨረባ በተባለው ስፍራ እራሱን አጥፍቷል። ግርማሜ ነዋይ ታህሳስ 17 ቀን አስከሬኑ በምንሊክ አደባባይ የተሰቀለ ሲሆን፤ በጎ አገራዊ ለውጥ የተጠሙት የወንድማማቾቹ ነፍሶች በልጅነታቸው ከመንደራቸው ቁልቁል ወርደው ይጫወቱበት በነበረው የጊዮርጊስ ፋፋ ላይ የወንበዴን ሞት በስቅላት ገመድ አስተናገዱት። የለውጡ ፍላጎት ሳያበቃ እነሱ አበቁ።

<u>ታህሳስ ግርግርንም ሆነ የካቲት 1966ን ሕዝባዊ አብዮት የወለደው የሕዝብ ብሶት ነው።</u> ዛሬ ታሪክን ለማጣመምና አቅጣጫ ለማሳት ተማሪ የለኮሰው ጣጣ፣ ግራው ኃይል ያመጣው ቁጣ፣ የያ ትውልድ መዘዝ እየተባለ ትውልዱን ተጠያቂ ማድረግ አግባብ አይደለም። ትውልዱ ለሀገሩ፣ ለሕዝቡ፣ ለድሃው መጮኹ አግባብ አልነበረም ካልተባለ በቀር "መሬት

**ላራሹ"፣ "ደሀ ይማር"፣ "የሀይማኖት እኩልነት ይጠበቅ"፣ "የሴቶች መብት ይረጋገጥ"፣ "የብሔር/ብሔረሰቦች መብት ይረጋገጥ"፣ "የዴሞክራሲ መብት ለሁሉም" እንደጮኸ፣ እንዳስተጋባ ነው ታሪኩ የሚዘግበው። ትውልዱ ይዞ በተነሳው ዓላማ አይወቀስም። አዎ የአካሄድ ስህተት ነበረበት? በሚገባ። ለራሳቸው በአገዛዝ እርከን ላይ ሆነው ፈላጭ ቆራጭ ሊሆኑ የሚችሉ የእነ ግርማሜ ነዋይ ደወል የቀሰቀሳቸውንና የጠራቸውን ለጭቁኖች እንደጮኹ ያንቀላፉ እነ ጥላሁን ግዛው፣ ዋለልኝ መኮንን፣ ማርታ መብራቱ፣ ቢንያም አዳነና በርካታ የዚያ ትውልድ ዕንቁዎች ታሪክ ድንቁርና እንደነበር ለመፃፍ ዛሬም ብዕር ብርታቱን ሲያገኝ ያሳዝናል።**

**"ያ ትውልድ ተቋም" በዘልማድ "የታህሳስ ግርግር" እየተባለ የሚታወቀውን እንቅስቃሴ ሃምሳ ሦስተኛ** (53ኛ) **ዓመት ምክንያት በማድረግ በወቅቱ የእንቅስቃሴው መሪ የነበሩትን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዙትን ወንድማማቾች ግርማሜ ነዋይንና ብርጋዴል ጄነራል መንግስቱ ነዋይን በማስታወስ ነው። መንግስቱ ነዋይ በመጨረሻው የፍርድ ውሳኔአቸው እንደተናገሩት** "…ከእናንተ ከዳኞቹና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ እኔ ፍርድ ተቀባይ የዛሬ ወንጀለኛ የነገ ባለታሪክ ነኝ፡፡" **አዎ "ያ ትውልድ ተቋም" የትላንቱ ባለታሪክ ወንድማማቾች፤ ለውጥ አራማጅ መሆን መስዋዕትነትን ጠያቂ መሆኑን ያስተማራችሁ፤ ታሪካችሁ ሕያው ነው እያልን ብርጋዴል ጄነራል መንግስቱ ነዋይ መጋቢት** 19 **ቀን** 1953 **ዓ.ም. የሞት ፍርድ ከተወሰነባቸው በኋላ የተናገሩት ንግግር እነሆ**!

"እናንት ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለ ይግባኝ ተቀብያለሁ፡፡ ይግባኝ ብየ ጉዳየን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ እንደማይሆን አውቃለውና በይግባኝ የአፄ ኃ/ስላሴን ፊት ማየት አልፈቅድም፡፡ በእግዚያብሄር ስም ተሰይማችሁ ከተቀመጣችሁበት የፍርድ ወንበር ላይ ከመቀመጣችሁ በፊት በእኔ ላይ የምትሰጡትን የዛሬውን ፍርድ ታውቁት እንደነበር ሳስብና ፍርድ እስከዚህ መርከሱን ስታዘብ ሀዘኔ ይበዛል፡፡

ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት፣ ነፃነትና እርምጃ የተነሳሁ ወዳጅ ነኝ እንጅ ለማፋጀት የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም፡፡ ይህንን ማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሰራዊትና መሳሪያ ሳላጣ ዛሬ እዚህ ከእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር፡፡

እኔ ከየአፄ ኃ/ስላሴ ድንክ ውሾች ያነሰ ደመወዝ የሚያገኙ ሁለት የተራቡ ወታደሮችን አጣልቼ ለማደባደብና አገር ለማፍረስ አለመምጣቴን የሚያረጋግጥልኝ እናንተ በትዕዛዝ ያገኛችሁትን ፍርድ ለመቀበል እዚህ መቆሜ ነው፡፡

ከእኔ በፊት በግፍ የፈሰሰው ንፁህ የኢትዮጵያዊያን ደም ብዙ ነው፡፡ በየአፄ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ግፍ ሽልማት በመሆኑ እኔ ለመሞት የመጀመሪያው ሰው አልሆንም፡፡ ስልጣን አላፊ ነው፡፡ እናንተ ዛሬ ከጨበጣችሁት የበለጠ ስልጣን ነበረኝ፡፡ ሀብትም አላጣሁም፡፡ ነገር ግን ህዝብ የሚበደልበት ስልጣንና ድሃ የማይካፈለው ሀብት ስላልፈለግሁ ሁሉንም ንቄ ተነሳሁ፡፡

አሁንም እሞታለሁ፡፡ ሰው ሞትን ይሸሻል ፡፡ እኔ ግን በደስታ ወደሞት እሄዳለሁ፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅነት ቀድመውኝ መስዋዕት የሆኑትን አብረውኝ ተነስተው የነበሩትን ጀግኖች ወንድሞቼን ለመገናኘት ናፍቄአለሁ፡፡
የጀመርኩት ስራ ቀላል አይደለም፡፡ አልተሸነፍኩም፡፡ ወገኔ የሆነው ድሃው የኢትዮጵያ ህዝብ የጀመርኩለትን ስራ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ፈፅሞ ራሱን በራሱ እንደሚጠቅም አልጠራጠርም፡፡ ከሁሉ በበለጠ የሚያስደስተኝ ለኢትዮጵያ ህዝብ ልሰራለት ካሰብኳቸው ስራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ወታደር ዋጋና ክብር ከፍ ማድረግ ሲሆን ይህ ሃሳቤ ህይወቴ ከማለፉ በፊት ሲፈፀም ማየቴ ነው፡፡

ዛሬ መኖራችሁን በማየቴ ነገ መሞታችሁን ረስታችሁ አሜን ብላችሁ ቀናችሁን በማስተላለፍ በመገደዳችሁ በእኔ ላይ ሳትፈርዱ በራሳችሁ ላይ የፈረዳችሁ መሆናችሁን አላስተዋላችሁም፡፡ እኔ የተነሳሁት ከትክክለኛ ህግና ከህሊናችሁ ውጭ ለመፍረድ እንዳትገደዱ ለማድረግ ነበር፡፡ በአጭሩ በእኔ ላይ ለመፍረድ የቸኮላችሁትን ያህል አስር እና አስራ አምስት ዓመት በቀጠሮ የምታጓላሉትን ህዝብ ጉዳይ እንደዚህ አፋጥናችሁ ብትመለከቱትና ብትሸኙት ኖሮ የእኔ መነሳት ባላስፈለገም ነበር፡፡

ከእናንተ ከዳኞቹና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ እኔ ፍርድ ተቀባይ የዛሬ ወንጀለኛ የነገ ባለታሪክ ነኝ፡፡ የኔ ከ ጓደኞቸ መካከል ለጊዜው በህይወት መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የመመዘኑን ፍርድ ለመጭው ትውልድ የሚያሳይ ይሆናል፡፡

**ዋ ! ዋ ! ዋ** ! *ለእናንተና ለገዢአችሁ፡፡* የኢትዮጵያ ህዝብ ሃሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚወርድባችሁ መዓት አሰቃቂ ይሆናል፡፡

በተለይ የአፄ ኃ/ስላሴ የግፍ መንግስት ባላደራዎች ሆነው ድህውን የኢትዮጵያ ህዝብ ሲገሸልጡት ከነበሩት መኮንን ሀ/ወልድና ገ/ወልድ እንግዳወርቅን ከመሳሰሉት በመንፈስ የታሰሩ በስጋ የኮሰሱ መዥገሮች መካከል ጥቂቶቹን ገለል ማድረጌን ሳስታውስና የተረፉትም ፍፃሜያቸውን በሚበድሉት በኢትዮጵያ ህዝብ እጅ ላይ መውደቅ ሲሰማኝ ደስ ይለኛል፡፡"

## ብርጋዴል ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ መጋቢት 22 1953 ዓ.ም. በስቅላት የሞት ፍርድ ሕይወታቸው አልፏል።



### <u>ዋቢ ጽሁፎችና መረጃዎች</u>

- የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966፤ 1989 ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ, አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፕሬስ አዲስ አበባ
- ኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ዶክመንተሪ፤ ያመኛው አገረ ገዥ፦ ግርማሜ ነዋይ
- ዊክፒዲያ (Wikipedia) እና ጐልጉል (Google)




### <u>ያ ትውልድ ተቋም ኢሜል</u>

yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com